

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከሜይ 1-10 የነበረው የአየር ሁኔታ እንዲሁም

## ከሜይ 11-20 እና ከሜይ 21-31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2025

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡ ፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 20.1፣ አዲስ አበባ ጥቁር እንበሳ 19.7 32.5፣ በአርባምንጭ 16.5፣ 15.7፣ ሀዋሳ 39.7፣ ደብረ ማርቆስ 31.5፣ 27፣ ቢሾፍቱ 30.2፣ ድሬ ዳዋ 20.4፣ 23.7፣ ጎሬ 20.2፣ ጅማ 45፣ መተሃራ 54.4፣ 28.6፣ ነቀምት 59.1፣ አቦምሳ 18.6፣ 88.7፣ አደሌ 20፣ አደት 17.4፣ አድዋ 24.2፣ አዲግራት 15.5፣ አይደር 16.5፣ ሐሮማያ 26፣ 17.2፣ አልም ከተማ 15.4፣ 26.5፣ አምቦ 18.9፣ 30.5፣ 22.5፣ 22.1፣ አምደ ወርቅ 32.9፣ አንገር ጉትን 20.4፣ አርጆ 18.8፣ 20.6፣ አርሲ ሮቤ 16.6፣ 48.2፣ አሶሳ 23.5፣ አዋሽ አርባ 18፣ አይሻ 26.6፣ ባቲ 29፣ 48፣ በደሌ 17፣ ብላቴ 19.2፣ 67.8፣ ቦሬ 18.1፣ 51.1፣ 18.1፣ 20.3፣ 19.6፣ ቡሂ 21.7፣ ቡርጂ 15.9፣ 16.3፣ ጨፋ 16.1፣ 15.7፣ ጭራ 27.7፣ 22፣ 26.4፣ ደባርቅ 19.4፣ 16.5፣ ደበረ ተቦር 15.2፣ ደምቢ ዶሎ 16.5፣ ዲላ 26.8፣ 19.4፣ 16፣ ዶሎ መና 20.8፣ 30.4፣ 40.3፣ ኢጃጂ 17.2፣ ፊቼ 26.1፣ ጋምቤላ 19.2፣ ገለምሶ 18.2፣ ወሊሶ 18.1፣ 18.5፣ ቡሌ ሆራ 35.8፣ 19.3፣ 31.2፣ ሐረር 23.9፣ ሆሳዕና 27፣17.3፣ 17.5፣ እምድብር 21.3፣ 22.6፣19.6፣ ጃራ 20.9፣ ጂንካ 35.7፣ ካቺሴ 32፣ ኮንሶ 16.2፣ 40፣ ቁሉምሳ 50.7፣ ሊሙ ገነት 17.2፣ ማይጨዉ 32.7፣ 29፣ማጀቴ 29፣ 21፣ ማጂ 24.7፣ መኢሶ 24፣ 16.5፣ መካነ ሰላም 16.2፣ 26.3፣ ምዕራብ አባያ 30.2፣ 17፣ ሞያሌ 20.3፣ 24.4፣ አዳማ 40.3፣ ንፋስ መዉጪያ 21፣ ሳዉላ 20.3፣ 28.2፣ 25.8፣ ሰንቃጣ 24.2፣ ሻምቡ 56.5፣ ሾላ ገበያ 20.4፣ 42.8፣ ስሪንቃ 70.2፣ ቴፒ 49.4፣ ተርጫ 24.6፣ 32.6፣ ጽጽቃ 37.8፣ ወራቤ15.2፣ 16.4፣ ወረኢሉ18.6፣ ወላይታ ሶዶ 30.4፣ 18.7፣ 17.1፣ 17.4፣ ያቤሎ 331፣ የትኖራ 16.4፣ ባቱ 26.6፣ አዋሮ 18.7፣ ኩረፋ ጨሌ 15.7 እንዲሁም ሽላቦ 26.5፣ 90.1 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ32 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-90.1 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል  ሽላቦ፣ አቦምሳ፣ ሲረንቃ፣ ብላቴ፣ ነቀምት፣ ሻምቡ፣ መተሃራ፣ ቦሬ፣ ቁሉምሳ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከሜይ 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ አሪ፣ ጋርዱላ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል  ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ኤረር እና የሲቲ፣ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን የደቡብ ጎንደር ዞኖች የሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከትግራ ክልል የመካከለኛዉ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ደዋና ሐረር ላይ ከ31-160 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ኮሬ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ፣ አሪ፣ ጋርዱላ ዞኖች ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ጅማ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ነጎብ፣ ጃራር፣ ኤረር፣ ፋፋን እና የሲቲ፣ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን የደቡብ ጎንደር ዞኖች የሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከትግራ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ቀልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ሃዉሲ እና የጋቢ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ደዋና ሐረር መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ




የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር

ከመደበኛ በታች መደበኛ ከመደበኛ በላይ

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ

በሌላ በኩል በአቦቦ፣ በአሶሳ፣ በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ በባቲ፣ በብላቴ፣ በቻግኒ፣ በጨፋ፣ በጨዋቃ፣ በድሬ ዳዋ፣ በፉኙዱ፣ በጋምቤላ፣ በገዋኔ፣ በጎዴ፣ ጎንደር፣ በቀበሪዳሀር፣ ላይብር፣ በመኢሶ፣ በመተሃራ፣ በመተማ፣ በምዕራብ አባያ፣ በሰመራ፣ በሻምቡ፣ በሽርቆሌ፣ ሸዋሮቢት እና በቴፒ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.2 እስከ 43.0 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የሜይ የመጀመሪያው አስር ቀናት የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ብለው ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ለተዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎችን የውኃ ፍላጎት ከማሟላት አንጻርም ሆነ ከሰኔ በኋላ ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረዉ ተስተዉሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በአንዳንድ እርጥበት አጠር በሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል፡፡

በሌላ በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በረባዳማ እና የአፈር ጸባያቸው ውሃን በማያሰርጉ እና በወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች በሚገኙ ማሳዎች ላይ መጠነኛ የሆነ የውሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እና በጎርፍ መጠረግ ሊያስከትል የሚችል አቅም እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታ (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሜይ አስር ቀናት በአብዛኛው አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ሰምጥ ሸልቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ፣ አይሻ፣ በላይኛው እና መካከለኛ ባሮ አኮቦ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ በላይኛው፣ በመካከለኛው እና በጥቂት ታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠኛ እጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት መካከለኛው ስምጥ ሸልቆ፣ በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ እና በጥቂት ላይኛው ምስራቃዊ ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገጸምድር ዉሃ ሀብት መጎልበት አስተዋፅኦ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ በታችኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ እንዲሁም በታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

ሜይ የበልግ ወቅት የመጨረሻ ወር ሲሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ መጠናከር ጋር ተያይዞ ዝናቡ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ በመሄድ ብዙ ቦታዎችን ይሸፍናል፡፡ በዚህም መሠረት አብዛኛው የኦሮሚያ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ የሲዳማ ክልል፣የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከ121-260 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ15-20 ቀናት ያህል ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይና የአማራ ምዕራባዊ ክፍልና የሱማሌ አካባቢዎች ከ41 እስከ 120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ለ10 ቀናት ያህል በአማካይ ያገኛሉ። ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በሜይ የመካከለኛው፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እስከ 30% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።


## 2.1 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሜይ የሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ  እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 1)። በመሆኑም በሚቀጥሉት አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም ከሳምንቱ አጋማሽ በኃላ አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን በማቋረጥ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የዝናብ ሥርጭት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት  ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ሜይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, የሚኖረወ የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና አሪ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ኤረር፣ ጃራር ዶሎ፣ ፋፊን እና ሲቲ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን እና የምዕራብ ጎጃም፣ የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች | ቀላል መጠን |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | |
|---|---|---|
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ


በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በሜይ የሁለተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በአፋር፣ በምዕራብ አማራ፣ በጋምቤላ፣ በሶማሌ እና በቤንሻንጉል-ጉሙዝና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት 29 ዲግሪ ሴልሺየስ እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ35 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 9)።




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሜይ 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ የሜይ ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሜይ የሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡብ፣ በደበብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምእራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10)፡፡




ካርታ 10 እ.ኤ.አ. ከሜይ 21-31, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.5 እ.አ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራትና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት እና ቀደም ብለዉ ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንሰሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩ አልፎ አልፎ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ለወቅቱ የእርሻ ስራ እንቅሥቃሴ አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም በተወሰኑ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሣዎች ላይ የውሃ መተኛትና የአፈር መታጠብን ሊያስከትል ይችላል። ባጠቃላይ በመጪው የሜይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች ያሉትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎጃም፣ የመካከለኛዉ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ አዊ ፣ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት ለመሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • የእርጥበት መብዛትን በማይቋቋሙ የአፈር ጠባይ ያላቸው ማሳዎች መጨቅየት እና የውኃ መተኛት<br>• ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ እንዲሁም የመሬት መንሸራተት | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር እርሻን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ማከናወን እና ዘር መዝራት<br>• የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል። |
| የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ዋግ ህምራ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖች አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት | • ከፍተኛ ትነት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መኖር | • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |



ስልክ+2511155383941ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ፣ የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፣ድሬደዋ እና ሐረሪ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ኤረር፣ ጀራር፣ ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለበልግ ሰብሎች እድገት<br>• ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• ከፍተኛ ትነት መኖር | • የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የማሳ ዝግጅት ማከናወን<br>• የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ሁሉም የሲዳማ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራትና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት<br>• የአፈርና የውሃ እቀባና የእርከንስራ ማከናወን |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ዶሎ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለተዘሩ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | • የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.6 እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ ሁለተኛ አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑት ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚጠበቀውን እርጥበት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሊኖር የሚችለው አሉታዊ ለመቀነስ እና ሊኖር የሚችለውን መልካም አጋጣም አልቆ ለመጠቀም እንዲቻለ ከታች የተቀመጡትን የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ በመተግበር የቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ

| ተፋሰሶች | የሚጠበቀው እርጥበት | አዎንታዊ ተፅዕኖ | አሉታዊ ተፅዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በመካከለኛ እና ታችኛው አሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አባይ እና ባሮ አኮቦ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ ክምችት መሻሻል | • ቅፅበታዊ ጎረፍ<br>• የውሃ በጎርፍ መበከል<br>• የደለል ስጋት<br>• የውኃ ወለድ በሽታዎች ስጋት መጨመር | • የፍሳሽ መውረጃዎች ማፅዳት<br>• የጎርፍ መቀልበሻ ቦይ እንዳሰፈላጊነቱ ማዘጋጀት<br>• የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም<br>• በጎርረፍ እንዲሁም በወንዝ ዳርቻ የሚኖሩ ግንዛቤ መስጠት ወይም ማስተጠንቀቅ<br>• ትንበያዎችን በቅርበት መከታተል<br>• የእርጥበት እጥረት ያለባቸው አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ማሰባሰብ |
| በመካከለኛው እና ታችኛው ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ አባይ፣ | ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍ ስጋት እና የመሬት መንሸራተት | • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማነስ<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብ እና ማጠራቀም<br>• የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከመሬት እና ጣራ ላይ የዝናብ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| በአብዛኛው በአይሻ፣ አፋር ደናከል፣ መረብ,ጋሽ፣ አዋሽ ተፋሰሶች | ደረቅ ሁኔታ | | • የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት<br>• ከፍተኛ ሙቀት | • ውሃን በቁጠባ መጠቀም<br>• ውሃን አክሞ ወይም አፍልቶ መጠቀም |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et